

ከችግሮች ጋር

ነብዩ (ሲ.ወ.ወ) ሙስሊም ላልሆኑ ሰዎች ሁልጊዜም ፍትሀዊ ነበሩ። እነሱን ወደ ኢስላም ለመጥራትና ችግሮቻቸውን ለማቃለል ነፍሳቸውን ሳይቀር ለመሰጠት ዝግጁ ናቸው። የሚያደርሱባቸውን መጥፎ ነገርና ጉዳት በትዕግስት ያሳልፉ ነበር። ለምን? አላህ "እዝነት አድርገን ላከንህ..." ብሏቸዋል። ለነማን? ለሙስሊሞች ብቻ? አይደለም "ለዓለም።"

አይሁዶችን አስቡ። ይሰድቧቸውና ተንኮል ያሴሩባቸው ነበር። እሳቸው ግን ለነሱ ጥሩ ሆነው ነው የቀጠሉት። አሚሻ (ረ.ዐ) ስትናገር አይሁዶች አንዴ በደጃችን እያለፉ ነበር። ለነብዩ "አሰም አለይኩም" ሞት ላንተ ይሁን አሏቸው። እሳቸውም "ወአለይኩም" በናንተም ላይ ይሁን አሏቸው። አሚሻ የሰማችው ነገር በጣም ስላናደዳት "ሞት ለራሳችሁ ይሁን። የአላህ እርግማንና ቁጣም ይውረድባችሁ" አለቻቸው። ነብዩም "አሚሻ ሆይ! ተይ። ብልህ መሆን አለብሽ። መራገምና መጥፎ ንግግር መናገር የለብሽም" አሏት። "የተናገሩትን ነገር አልሰሙም እንዴ?" አለቻቸው። "እኔ የተናገርኩትንስ አልሰማሽም? ዱዓ አድርጌባቸዋለሁ። ያ ዱዓ ተቀባይነት አለው። እነሱ በኔ ላይ ያደረጉት ዱዓ ግን ተቀባይነት የለውም" አሏት።

አዎ! ከፋትን በክፋት መመለስ አስፈላጊ አይደለም። አላህ "ሰዎችን በመልካም ቃላት አናግሩ..." ይላል። በአንድ ወቅት ነብዩ (ሲ.ወ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ከዘመቻ እየተመለሱ ነበር። ዛፎች በበዙበት አንድ ሸለቆ ውስጥ ሲደርሱ እረፍት ለማድረግ ወሰኑ። ተበታትነው በየዛፉ ስር ተኙ። ነብዩም ሰይፋቸውን ዛፍ ላይ ሰቅለው ተኙ። ለካስ አንድ ኃይማኖት የለሽ ሰው ይከታተላቸው ኖሯል። ቀስ ብሎ ተጠጋቸው። ሰይፋቸውን ከዛፉ ላይ አውርዶ ያዘና "ሙሐመድ ሆይ! ዛሬ ከኔ የሚያድንህ ማን ነው?" ሲል ጮኸባቸው።

ነብዩ (ሲ.ወ.ወ) ከእንቅልፋቸው ነቁ። ሰውዬው ሊገድላቸው ተዘጋጅቷል። አጠገባቸው ሰው የለም። ጓደኞቻቸው በሙሉ በየዛፉ ስር ተበታትነው እንደተኙ ናቸው። ሰውዬው በሀይሉና በጥንካሬው በመመካት በተደጋጋሚ "ከኔ የሚያድንህ ማን ነው?" "ከኔ የሚያድንህ ማን ነው?" ይላቸዋል። እሳቸውም "አላህ" ይሉታል። ሰውዬው በድንገት በፍርሀት ተዋጠ። ሰይፉ ከእጁ አምልጦት ወደቀ። ነብዩ ሰይፉን አነሱና "ከኔ የሚያድንህ ማን ነው?" አሉት። እየተንቀጠቀጠ እንዲያዝኑለት ይጠይቃቸው ጀመር። "ማንም የሚጠብቀኝ የለም። እባክህን እዘንልኝ" አላቸው።

ነብዩም "ትሰልማለህ?" በማለት ጠየቁት።

"አልሰልምም። ነገር ግን እርስዎን ከሚዋጋ ማንኛውም ቡድን ጋር አልወግንም!" አላቸው። ይቅርታ አደረጉለት። ሰውዬው የአንድ ህዝብ መሪ ነው። ሄዶ ህዝቦቹን ወደ ኢስላም ጠራቸው። ሁሉም ሰለሙ። አዎ ለሰዎች ጥሩ ሁን። ልባቸውን ያዝ።

በእርግጥም ነብዩ ከቀንደኛ ጠላቶቻቸው ጋር ሳይቀር ያልተበረዘ ባህሪ ነበራቸው። በዚህም ያሸንፏቸዋል። ልባቸውን ይማርካሉ። ከኩፍር ያፀዷቸዋል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቢይፋ ሰዎችን ወደ ኢስላም መጣራት ሲጀምሩ ቁረይሾች አጥብቀው ይቃወሟቸው ነበር። ተሰባስበው ስለ ነብዩ ጥሪ፣ ሰዎች በፍጥነት እየተቀላቀሏቸው ስለመሆኑና እነሱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይወያዩ ነበር። ከመካከላችን በአስማት፣ በትንቢት ተናጋሪነትና በግጥም አሉ የተባሉ ሰዎችን እንፈልግ። ከዚያም ደረጃችንን ዝቅ ያደረገውን፣ ያለያየንን እና ኃይማኖታችንን ያንቋሸሸውን ሰው እናነጋግረውና የሚለውን እንስማ ተባባሉ። ኡትባ ቢን ረቢዓን መረጡ። ለኡትባም "አቡል ወሊድ ለዚህ ተስማሚ ሰው አንተ ነህ" ይሉታል። ኡትባ ታጋሽ ሰው ነው። እሱም "ቁረይሾች ሆይ! እሱ ዘንድ ሄጄ እንዳናግረውና ምናልባትም ማባበያዎችን አቅርበንለት ያሻውን እንዲወስድ ፈለጋችሁ?" አላቸው።

"አዎ! አቡል ወሊድ" አሉት። ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሄደ። ቁጭ ብለው አገኛቸው። "መሐመድ ሆይ! ከአንተና ከአብዱላህ ማን ይበልጣል?" አላቸው። ነብዩም አባታቸውን በማክበር ዝም አሉት።

"ከአንተና ከአብዱል ሙጠሊብስ ማን ይበልጣል?" አላቸው። አሁንም አያታቸውን በማክበር ዝም አሉት።

"እነሱ ይሻላሉ ብለህ የምታስብ ከሆነ አንተ የሰደብካቸውን አማልዕክት እንዴት ሊያመልኩ ቻሉ? ከነሱ እኔ እሻላለሁ ብለህ የምታስብ ከሆነ ደግሞ ተናገር፤ የምትለውን እንስማህ" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መልስ ከመስጠታቸው በፊት ኡትባ በቁጣ ጠፈና "ወላሂ እንዳንተ በዚህ ሕዝብ ላይ ችግር የፈጠረ ሰው አላየንም። ለያዬኸን፤ ደረጃችንን ዝቅ አደረግክ፤ ኃይማኖታችንን አንቋሸሽክ፤ ከፍተኛ ችግር አደረስክብን። ሰዎች ምን እያሉ እንደሆነ ታውቃለህ። ሰይፎቻችንን ስለን እርስ በርስ ከመገዳደል ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም እያሉ ነው" አላቸው። ኡትባ ሲደነፋ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተረጋግተው ቁጭ ብለው አደመጡት። ሊደራደራቸው ወሰነና "ይህን ሁሉ የምታደርገው ሀብት ፈልገህ ከሆነ ተባብረን የቁረይሽ ሀብታሞች ካላቸው የበለጠ ሀብት እንስጥህ። ስልጣን ከፈለግክ አለቃችን እናድርግህ። ንግስናም ቢሆን ልንሰጥህ ዝግጁ ነን። እርኩስ መንፈስ ተጠናውቶህ ከሆነና ከላይህ ላይ ማስወገድ ካልቻልክ ደግሞ ጥበበኛ ሀኪም ጠርተን እናሳክምህ...።" ኡትባ ይህንን ሰነ ምግባር የጎደለው

ንግግር በሚናገርበት ጊዜ ነብዩ ጸጥ ብለውና ተረጋግተው ያዳምጡታል። የስልጣን፣ የሀብት፣ የሴትና የአዕምሮ ሕክምና ስጦታዎቹን ከዘረዘረ በኋላ መልስ በመሻት ዝም አለ። ነብዩም "አቡል ወሊድ ሆይ! ጨረስከ?" በማለት ጠየቁት።

"አዎ" አላቸው።

"አሁን እኔን አዳምጠኝ" አሉት። "እሺ" አለ።

ነብዩም "በአላህ ስም ሩህሩህና አዛኝ በሆነው። ሀሚም። /ይህ ቁርዓን/ እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ ከሆነው /አላህ/ የተወረደ ነው። አንቀፆቹ የተብራሩ የሆነ መፅሐፍ ነው። አረብኛ ቁርዓን ሲሆን ለሚያውቁ ህዝቦች /የተብራራ/ ነው። አብሳሪና አስፈራሪ ሲሆን /ተወረደ/። አብዛኞቻቸውም ተውት። እነሱም አይሰሙም።" ነብዩ አንቀጹን ማንበብ ቀጠሉ። ኡትባ ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ጀመር። እጆቹን ወደ ኋላ አድርጎ ተደገፋቸውና አንቀፆቹን ያዳምጣል። ነብዩም ከቀጣዩ አንቀፅ እስኪደርሱ ድረስ ማንበባቸውን ቀጠሉ። "/ከእምነት/ እንቢ ቢሉም እንደ አድና ሰሙድ መቅሰፍት ቢጤ የሆነን መቅሰፍት አስጠነቅቃችኋለሁ በላቸው።"

ኡትባ ማስጠንቀቂያውንና የቅጣት ማስፈራሪያውን ሲሰማ ልቡ ፈራ። ዘሎ ተነሳና አፋቸውን በእጁ ያዛቸው። ነገር ግን ነብዩ ሱጁድ እስከሚያስደርገው አንቀጽ ድረስ አነበቡ። ሱጁድም አደረጉ። ከሱጁድ ተነሱና ትኩር ብለው እየተመለከቱት "ኡትባ ሆይ! ሰማህ አይደል?" አሉት። "አዎ" አላቸው። "ምርጫው የራስህ ነው" አሉት። ኡትባ በጉጉት ወደሚጠብቁት ጓደኞቹ ሄደ። እየቀረባቸው ሲሄድ እርስ በርስ "በአላህ እንምላለን፤ የተለዬ ስሜት ይዞ ነው የተመለሰው" ይባባላሉ። አጠገባቸው ሲደርስ "ምን ተፈጠረ አቡል ወሊድ?" አሉት።

"ከዚህ በፊት ሰምቻቸው የማላውቃቸውን ቃላት ሰማሁ። ወላሂ የግጣሚዎች፣ የአስማት ወይም የጥንቆላ ቃላት አይደሉም። ቁረይሾች ሆይ! ምክሬን እንድትሰሙና ከግቦቹ ይደርስ ዘንድ ለዚህ ሰው ሙሉ ነፃነት ትሰጡት ዘንድ አጠይቃችኋለሁ። በዚህ መልኩ ብቻ ነው ራሳችሁን ከእሱ ጋር በሰላም ማለያየት የምትችሉት። እምላለሁ ንግግሮቹ አንድ ቀን የበላይ ይሆናሉ። ሰዎች ሆይ! እንዲህ ሲል ሰምቼዋለሁ፦ "በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህና በጣም አዛኝ በሆነው። ሀሚም። /ይህ ቁርዓን/ እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ ከሆነው /አላህ/ የተወረደ ነው። እንደ አድና ሰሙድ መቅሰፍት ቢጤ የሆነን መቅሰፍት አስጠነቅቃችኋለሁ" ይህንን ሲናገር አፉን በእጄ ያዝኩት። በዝምድናችን ይሁንበህ አቁም ስል ለመንኩት። ሙሐመድ ሲናገር እንደማይዋሽ ታውቃላችሁ። ቅጣት እንዳይወርድባችሁ እፈራለሁ" አላቸው። አቡል ወሊድ ፀጥ ብሎ ያስተነትን ጀመር። ጓደኞቹ ትኩር ብለው ይመለከቱታል። "በአላህ እምላለሁ ንግግሩ መንፈስ የሚማርክ ውበት አለው። ሰሩ የለመለመ ጫፉ የሚያፈራ ነው። ሰው ይህን ሊል

አይችልም። ሰው ይህን ሊል አይችልም" አላቸው።

"ይሄማ ግጥም ነው አቡል ወሊድ፤ ግጥም ብቻ" አሉት። "ወላሂ ስለ ግጥምና ስለ ግጥም ቤት አመታት ከኔ በላይ እውቀት ያለው ሰው የለም! የጅኖችን ግጥም ሳይቀር አውቃለሁ። ወላሂ የሱ ንግግር ከማንኛውም ዓይነት ግጥም ጋር አይመሳሰልም!" ኡትባ ስለ ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ማውራቱን ቀጠለ። ምንም እንኳ ባይሰልምም ነፍሱ ወደሱ ለማጋደሏ ምንም ጥርጥር የለውም። የነብዩ ድንቅ ባህሪና ጥሩ አድማጭነት በኡትባ ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳሳደረ ተመልከት። ምንም እንኳ እሱ የኢስላም ቀንደኛ ጠላት ቢሆንም። በሌላ ጊዜ ቁረይሾች የነብዩ ባልደረባ የሆነው የኢምራን ቢን ሁሰይን አባት ሁሰይን ቢን አልሙንዚር አል ኹዛኢን ላኩ። ከነብዩ ጋር ተወያይቶ የጀመሩትን ነገር ሊያስቆም መጣ። እናም የተለመደውን የቁረይሾች ምሬት በመድገም "ሊያዬኸን፤ ደረጃችንን ዝቅ አደረግክ..." ወዘተ አላቸው። ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ተረጋግተው ካዳመጡት በኋላ በትህትና "ጨረስክ አባ ኢምራን?" አሉት። "አዎ" በማለት መለሰ። "ለምጠይቅህ ጥያቄ መልስ ስጠኝ" አሉት። "እሺ" አላቸው።

"አቡ ኢምራን ሆይ! ስንት አማልዕክት ነው የምታመልከው?" አሉት። "ሰባት። ስድስት መሬት ላይ ያሉ አንዱ ደግሞ ሰማይ ላይ ያለ" አለ። "የምትወደውና የምትፈራው የትኛውን ነው?" አሉት።

"በሰማይ ላይ ያለውን" አለ። ነብዩም በሙሉ ትህትናቸው "ሁሰይን ሆይ! ኢስላምን የምትቀበል ከሆነ ጠቃሚ የሆኑ ሁለት ቃላትን አስተምርሃለሁ" አሉት። ሁሰይን ኢስላምን ወዲያው ተቀበለና "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አስተምርሃለሁ ያሉኝን ሁለት ቃላት ያስተምሩኝ" አላቸው። ነብዩም "አላህ ሆይ! ወደ ቀጥተኛው መንገድ ምራኝ። በራሴ ላይ ከማመጣው መጥፎ ጠብቀኝ በል" አሉት።

ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ሰዎችን የሚያናግሩበት መንገድ ሁሌም ምርጥ ነው። ባህሪያቸው በአስደናቂ መልኩ በሰዎች ላይ በጎ ተጽእኖ ያሳድራል። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን ወደ ኢስላም በማምጣቱ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

አንድ ወጣት ለትምህርት ጀርመን አገር በመሄድ አንድ የጋራ ህንፃ ውስጥ ይኖራል። አንድ ጀርመናዊ ጎረቤት ነበረው። ቤታቸው ጎን ለጎን ከመሆኑ ውጪ ሁለቱን ምንም የሚያገናኛቸው ነገር የለም። ጀርመናዊው በድንገት ወደ ሌላ አገር ይሄዳል። አንድ ጋዜጣ አከፋፋይ በየቀኑ እየመጣ በሩ ስር ጋዜጣ ያስቀምጥለታል። ወጣቱ ጋዜጦቹ በር ላይ ተከማችተው ሲያይ ጀርመናዊው ወደ ሌላ አገር መሄዱን አወቀ። ጋዜጦቹን ሰብስቦ ቤቱ ወስዶ አስቀመጠለት። በየቀኑ እያነሳም ያስቀምጥለት ጀመር። ጀርመናዊው ከሁለት ወር በኋላ ተመለሰ። ወጣቱ ሰላም ካለው በኋላ

"የዜና ዘገባዎችን ትከታተላለህ። ወይም ቢጋዜጣው ላይ የሚካሄዱ ውድድሮችን ትሳተፍ ይሆናል በሚል ግምት እንዲያመልጥህ ስላልፈለኩ አስቀመጥኩልህ" በማለት ጋዜጦቹን ሰጠው። በሁኔታው የተገረመው ጀርመናዊው "ላደረግከልኝ ውለታ ገንዘብ ልከፈልህ?" ሲል ጠየቀው። "ኃይማኖታችን ለጎረቤቶቻችን መልካም እንድንውል ያዘናል። ላንተ ለጎረቤቴ ደግ የመሆን ግዴታ አለብኝ" አለው። የቅርብ ጓደኛሞች ሆኑ። በመጨረሻም ጀርመናዊው ሰለመ።

ሀዲሴ...

ጥሩ ዳዒ ማለት ከቃሉ በፊት በድርጊቱ ዳዕዋ የሚያደርግ ነው።



ከእንስሳት ጋር

ጥሩ የአቀራረብ ጥበብ የአንድ ሰው ልምድ ሲሆን ሁለተኛ ተፈጥሮውና የስብዕናው አንድ አካል ይሆናል። የዚህ ዓይነት ሰው ሁሌም ለመቅረብ የሚቀል፣ ልቡ አዛኝ፣ አዕምሮው አስተዋይ፣ ከሰው ልጅ አልፎ ለእንስሳትና ለአፅዋትም ሳይቀር አሳቢ ይሆናል።

አንዴ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር እየተጓዙ ሳለ መንገድ ላይ ያርፋሉ። ሶሃቦችም ሁለት ጫጩቶችን የያዘች አንዲት ወፍ ተመለከቱ። ጫጩቶቿን ወሰዱባት። ወፏ ከንፎቿን እያውለበለበች ትዘራቸው ጀመር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲመጡ የሆነውን ነገር ተመለከቱ። ለልደረቦቻቸውም "ጫጩቶቿን ወስዶ ይህችን ወፍ ያሳዘነ ማነው? ቶሎ መልሱላት" አሉ። በሌላ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተቃጠለ የጉንዳኖችን መኖሪያ ተመለከቱ። "ይህን የጉንዳኖች መኖሪያ ያቃጠለው ማነው?" በማለት ጠየቁ። አንዱ ባልደረባቸው "እኔ ነኝ" አላቸው። ነብዩ ተቆጡና "ከአላህ በስተቀር በእሳት የሚቀጣ የለም" አሉ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አዛኝ ናቸው። ኡዱ ሲያደርጉ ድመት ካዩ የኡዱ እቃውን መሬት ላይ ያስቀምጡላታል። ጠጥታ ስትጨርስ በተረፈው ውሃ ኡዱ ያደርጋሉ።

አንዴ አንድ ሰው በጉን መሬት ላይ ኢጋድሞ አንገቱን በእግሩ ከረገጠ በኋላ ቢላውን ይሰላል። ይህን የተመለከቱት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጣም ተናደዱና "ሁለቴ እንዲሞት ትፈልጋለህ? በጉን መሬት ላይ ከማጋደምህ በፊት ለምን ቢላውን አልሳልከም?" በማለት ተቆጡት። በሌላ ጊዜም እንዲሁ ሁለት ሰዎች ግመሎቻቸው ላይ ቁጭ ብለው ሲያወሩ ተመለከቱ። ግመሎቹ አሳዘኗቸውና ሰዎች እንስሳትን እንደ ወንበር እንዳይጠቀሙ ከለከሉ። ማለትም ጉዞ ሊጀምሩ ሲሉ ብቻ

እንዲጋልቧቸውና ተልዕኳቸውን ሲፈጽሙ እንዲወርዱና እንስሳቱን እንዲያሳርፉ አዘዋል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከእንስሳት ፊት ላይ ንቅሳት ማድረግንም ከልክለዋል።

ነብዩንና አል አዝባ የተባለች ግመላቸውን የተመለከተ አንድ ታሪክ አለ። በአንድ ወቅት ካፊሮች መዲና ውስጥ አዝባን ጨምሮ የሙስሊሞችን ግመሎች

በሙሉና አንዲት ሙስሊም ሴትን ጠልፈው ወሰዱ። ብዙ ከተጓዙ በኋላ አንድ ቦታ ላይ አረፉ። እንቅልፍ ወሰዳቸው። ሴትዮዋ ለማምለጥ ወሰነች። ግመሎቹ ተዘዋውረው ይመገቡ ዘንድ ፈትተዋቸዋል። አንዷን ግመል ለመጋለብም አሰበች። ቀስ ብላ ግመሎቹን ስትጠጋቸው ድምጽ ያሰሙባታል። ሁሉንም ካዳረሰች በኋላ ወደ አዝባ ስትጠጋ በሚገባ የሰለጠነች ሆና አገኘቻት። እሷን ጋልባ ወደ መዲና መንገዷን ቀጠለች። ማምለጧን ስታረጋግጥ በደስታ ተሞልታ "ጌታዬ ሆይ! በዚህች ግመል ሰበብ ካተረፍከኝ ይህችን ግመል ልሰዋልህ ቃል እገባለሁ" አለች።

መዲና ስትደርስ ሰዎች ግመሏ የነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) መሆኗን አወቁ። እናም ወደሳቸው ወሰዷት። ኋላ ላይ ሴትዮዋ መጣችና ግመሏን ላርዳት ነው አሏቻቸው። ነብዩም "ለዋለችልሽ ውለታ ልትሰጫት የሚገባው ምንዳ ይሄ ነው እንዴ? አላህ በሷ ሰበብ ጠበቀሽ። ከዚያ እሷኑ ልታርጃት ፈለግሽ?" አሏት። ከዚያም "ስለት አላህን ባለመታዘዝ ከሆነና የራስ ባልሆነ ንብረት ላይ ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም" አሏት። እንደ አስተዋይነት እና ቸርነት ያሉ ጥበባትን ለምን ተፈጥሯዊ ባህሪህ አታደርጋቸውም? ከእንስሳት፣ ከእፅዋትና ህይወት ከሌላቸው ነገሮች ጋር ባለህ ግንኙነት ሳይቀር ተግባራዊ የምታደርጋቸውና ሁሌም አብረውህ የሚኖሩ ተፈጥሯዊ ባህሪያት። ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) መስጊዳቸው ውስጥ የጁመዓ ኹጥባ የሚያደርጉት የቴምር ዛፍ ግንድ ተደግፈው ነበር። አንዲት አንሷር "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ቁጭ የሚሉበት ነገር ላዘጋጅልዎት። የአናፂነት ሞያ ያለው ባሪያ አለኝ" አሏቻቸው።

ነብዩም "እሺ" አሏት።

ሚንበር አዘጋጀችላቸው። በቀጣዩ አርብ ሚንበሩ ላይ ተቀመጡ። ከኋላቸው ያለው የዛፍ ግንድ ሲጢጥ የሚል ድምፅ ያሰማ ጀመር። መስጊዱ ተንቀጠቀጠ። ግንዱ እንደ ህፃን ልጅ አለቀሰ።

ነብዩ ከሚንበሩ ወርደው እቅፍ አደረጉት። "የመሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። ባላቅፈው ኖሮ የፍርዱ ቀን ድረስ ያለቅስ ነበር" አሉ።

አንድ ፍንጭ

አላህ ሰውን ከፍ አድርጎታል። ሆኖም ይህ ሌሎች ፍጥረታትን የመጨቆን አድል አይሰጠውም።



የሰውን ልብ ለማሸነፍ የሚያስችሉ ዘዴዎች

በአንድ የተወሰነ ተግባር ላይ በመሳተፍ ላይ ያለ ሰው ዓላማዎቹን ለማሳካት ልቆ ለመገኘት ይጥራል። ሀብት የሚወድ ሰው እንዴት እንደሚያካብተው ይማራል። ንግድ ላይ እንዴት ማጭበርበር እንደሚችል የሚማርም አይጠፋም። የሳተላይት ቴሌቪዥን ቻናሎች የተለያዩ ፕሮግራሞችን በአዲስ ቴክኖሎጂ አየር ላይ በማዋል ተመልካቾችን ለመሳብ ጥረት ያደርጋሉ። ወደፊት ለሚያቀርቧቸው ፕሮግራሞቻቸው አቅራቢዎቻቸውን ተመልካቾችን በመሳብ ጥበብ ያሰለጥናሉ። ጋዜጦች፣ ሬዲዮኖችና ቴሌቪዥኖችም እንዲሁ። የተለያዩ ምርቶችን የሚሸጡ ሰዎችም ይህንኑ ያደርጋሉ። (ሀራምም ይሁን ሀላል።) እነዚህ ሰዎች ሁሉ በተሰማሩበት መስክ ሁሉ የበላይ ለመሆን የሚያስችላቸውን ዘዴ ለመያዝ ጥረት ያደርጋሉ።

አርባ ሰዎች ተሰባስበው ባሉበት ክፍል ውስጥ ገባህ እንበል። ሁሉንም ሰዎች ሰላም እያልክ ስታልፍ የመጀመሪያው ሰው እጅህን ቀስ ብሎ ጨብጦ ቅዝቅዝ ያለ ሰላምታ አቀረበልህ። ሁለተኛው ሰው ደግሞ አጠገቡ ካለው ሰው ጋር እያወራ ፊቱን እንዳዞረ ሰላም ካለህ በኋላ ወሬውን ቀጠለ። ሶስተኛው ሰው ስልክ እያናገረ በመሆኑ ምንም አይነት ቃል ሳይተነፍስና አክብሮት ሳያሳይህ እጁን ብቻ ዘርግቶ ሰላም አለህ። አራተኛው ሰው ከመቀመጫው በፍጥነት ተነስቶ እቅፍ አድርጎ ሳመህ። እንኳን ደህና መጣህ ብሎ ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረበልህ። ፊቱ በፈገግታ ተሞልቷል። ምንም እንኳን ሁላታችሁ ከዚህ በፊት የማትተዋወቁ ቢሆንም አንተን በማግኘቱ መደሰቱን ያሳያል። ከዚያ ቀሪዎቹን ሰዎች ሰላም ብለህ ተቀመጥክ። ልብህ ለአራተኛው ሰው የላቀ ክብር መስጠቷን ትጠራጠራለህ? አትጠራጠር። ምንም እንኳ ስሙን፣ ደረጃውንና ሰራውን ወዘተ የማታውቀው ቢሆንም በተሳካ ሁኔታ ልብህን አግኝቷል። በሀብት፣ በደረጃ፣ ወይም በዝምድና ሳይሆን በመግባባት ጥበብ ብቻ።

ልብ በጉልበት፣ በሀብት፣ በወንበትና በደረጃ አይሸነፍም። ልብ የሚሸነፈው በጣም በትንሽ መስዋዕት ነው። ማሸነፍ የሚችሉት ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው። በከፍተኛ ድብርት የተነሳ የስነልቦና ህመም የገጠመውን አንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዬን አስታውሳለሁ። አባቱ በፖሊስ ኃይል ውስጥ ትልቅ ባለስልጣን ነው። ለጥቂት ጊዜያት ያህል ወደ ዩንቨርሲቲው እየመጣ ልጁን እንድረዳለት ይጠይቀኝ ነበር።